## ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ በኢትዮጵያ የሕግ አወጣጥ ሥርዐት

## ክፍል አንድ ።

## የሕግ አወጣጥ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግሥት

* በሺፈራው ወልደ ሚካኤል

ይህ ጽሑፍ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግሥት በሥልጣን በቆየ ባቸው ጊዜያት በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረውን የሕግ አወጣጥ ሥርዐት ለማሳየት ይሞክራል ። በጊዜ ሲሰላ ጽሑፉ ከመስከረም 2 ፡ 1967 ዓ.ም. እስከ መስከረም 1980 ዓ.ም. ያለውን ወቅት የሚያካትት ይሆናል ።

በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ የሕግ አወጣጥ የተለያዩ ደረጃዎች አሉት ፤ ማለ ትም ፡ የሕግ ማመንጨትን ፣ ማጠናቀርን ፡ ማጽደቅን ፡ መፈረምንና ፣ ማወጅ ያጠቃልላል ። ርዕሱን ከነዚህ ነጥቦች አኳያ ለመዳሰስ እንሞክራለን ።

የአብዛኛዎቹ ሀገሮች ሕገ መንግሥቶች በጽሑፍ የሠፈሩ ናቸው ፤ እነዚህም ሕግጋተ መንግሥት አብዛኛውን ጊዜ የሕግ አወጣጥን ማለትም ሕግ በማን እንደሚወጣ ፤ በአወጣጡም ሥርዐት ሊከተሉዋቸው ስለሚገቡ ቅደም ተከ ተሎች (በፓርላማ የሚወጣ ሲሆን ማለት ነው) ወይም ሊከተሏቸው (በዘውዳዊ አገዛዝ የሚወጣ ሲሆን) ስለሚገቡ ደንቦች ይደነግጋሉ ። በኢትዮጵያም ቢሆን ይህ ሁኔታ ከ1920ዎቹ ጀምሮ እስከ መስከረም 2 ፡ 1967 ዓ ም ድረስ የነበረ ሐቅ ነው ። ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግሥት የኃይለ ሥላሴን ዘውዳዊ አገዛዝ አስለቅቆ ሥልጣን እንደጨበጠ መስከረም 2 ፡ 1967 ዓ ም በአዋጅ ቁ. 1/1967 መሠረት የ1948ቱን ሕገ መንግሥት እንዳይሠራ አደረገ ።[1] በተጨማሪም የሕግ መምሪያንና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤቶችም (ፓርላማ) እንዲፈርሱ ሆነ ።[2] በዚ ሁም የተነሳ ከ1967 ዓ ም ወዲህ ላሉት ጊዜያት በኢትዮጵያ ላለው የሕግ አወጣጥ የ1948ቱ ሕገ መንግሥት ምንም ሕጋዊ ጠቀሜታ የለውም ።

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግሥት ስለሕግ አወጣጥ ጉዳይ የሚያሳይ ቀጥተኛና ብቸኛ ሕግ እንዳላወጣ የታወቀ ቢሆንም ስለዚሁ ጉዳይ ፍንጭ የሚ ሰጡ ጥቂት ሕጎች እንዳሉ ይታመናል ። በጸሐፊው አስተያየት የጊዜያዊ ወታደ ራዊ አስተዳደር ደርግንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣን እንደገና ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁ. 110/1969 ለዚሁ ጉዳይ ዋነኛው ነው ። የአዋጁ አንቀጽ 5/6/ የደርግ ጉባኤ አዋጆችን እንደሚያወጣ ደንግጓል ።[3] ስለሆነም የበላይ ሕጎችን (አዋጆችን) የማውጣት ሥልጣን የደርጉ ጉባኤ መሆኑ የታመነ ነው ። ከዚሁ አዋጅ አንቀጽ 19[4] መገንዘብ እንደምንችለው ሚኒስትሮችና ኮሚሺነሮች ሕግ ማመን ጨት ብቻ ሳይሆን ደንቦች የማውጣት ሥልጣንም እንደተሰጣቸው ነው ። ይህም የተለመደ አሠራር ነው ። ለምሳሌ የሠራተኛ ማኅበራት አዋጅ ቁ. 222/1974[5] ዓ. ም. የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርን ደንቦች የማውጣት ሥልጣን አጐና ጽፎታል ። የውሃ ሀብት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 21/1973[6] አንቀጽ 15ም ለውሃ ሀብት ኮሚሽኑ ደንብ የማውጣት ሥልጣን ሰጥቶታል ።

ሕግ የማመንጨቱ ሥልጣን ለአንዳንድ ሕዝባዊ ድርጅቶችም ቢሆን ተሰጥ ቶአል ። በዚሁ ጉዳይ የሠራተኛ ማህበራት አዋጅ ቁ. 222/1974 ዓ ም አንቀጽ5/12 እንደምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል ። ይኸው አንቀጽ እንደሚከተለው ይነበባል ።

5/ የሠራተኞች ማኅበር የወል ተግባርና ኃላፊነት አግባብ ባለው ሌላ ሕግ የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሠራተኞች ማኅበር የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል ።

12/ የመንግሥት ሕጎች ፤ ደንቦች ፡ መመሪያዎችና ፡ መግለጫዎች በአባሉ እንዲታወቁ እንዲከበሩና በተገቢ ሁኔታ በተግባር ላይ እንዲውሉ ማድረግ ፤ ሠራተኞችን የሚመለከቱ አዳዲስ ሕጎችና ደንቦች እንዲወጡ የወጡትም እንዲሻሻሉ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን ጠብቆ ሐሳብ ማቅረብ (ሠረዝ የተጨመረ) ።

የመላው ኢትዮጵያ ገበሬዎች ማኅበርም ቢሆን ገበሬውን በሚመለከት በሚወጡ ሕጎች ላይ የተወሰነ ሚና እንዲኖረው ተደርጓል ። ይህም የገበሬ ማህበራትን ለማጠናከር በወጣው አዋጅ ቁ. 223/1974 [7] በአንቀጽ 30/3/ በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል ። አንቀጽ 30/3/ በከፊል እንደሚከተለው ይነበባል ።

(3) ገበሬውን የሚመለከቱ ደንቦችና መመሪያዎች ሲወጡ ሃሳብ የማቅረብ . . . (ሠረዝ የተጨመረ) ።

ማእከላዊዎቹ የከተማ ነዋሪዎች ማህበራትም ቢሆኑ ሕግ የማመንጨትና አንዳንዴም ደንብ የማውጣት ሥልጣን ተሰጥቶአቸዋል ። [8] ሕግ የማመንጨቱ ሥልጣን ቻርተር ለተሰጣቸውም ሆነ ላልተሰጣቸው ከተሞች የተሰጠ ሥልጣን ነው ። በዚሁ ነጥብ ጠቃሚዎቹ የሕግ አንቀጾች በአንቀጽ 39 ሥር ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ናቸው ። እንደሚከተለውም ይነበባሉ ።

1. ከተማው ቻርተር የተሰጠው ሲሆን ፤

ሀ/ የሚኒስትሮች ምክር ቤትን በማስፈቀድ የቦታ ኪራይ ፤ የአገልግሎት ታክስ ፤ የቤት ግብርና ቀረጥ መደልደል ፤ መሰብሰብ ፤

ለ/ ስለከተማው አስተዳደርና ስለማኅበሩ ንብረት አጠባበቅ ስለከተማው ጸጥታና ስለሕዝቡ ጤንነት የሚኒስትሮች ምክር ቤትን በማስፈቀድ ደንብ ማውጣት ፤

ሐ/ የከተማውን ፕላን አዘጋጅቶ ለመንግሥት ማቅረብ ፤ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ማዋል ፤ የከተማውን ቦታ በፕላን መሠረት ማስተዳደር ፤

2. ከተማው ቻርተር ያልተሰጠው ሲሆን ፤

ሀ/ የቦታ ኪራይ ፡ የአገልግሎት ታክስ የቤት ግብርና ቀረጥ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ ማቅረብ ሲፈቀድም መሰብሰብ ። (ሠረዝ የተጨመረ) ።

ለ/ የከተማውን ፕላን አዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ ማቅረብ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ማዋል የከተማውን ቦታ በፕላን መሠረት ማስተዳደር ።

የከተማ ነዋሪዎች ማኅበራቱ ይህንን እላይ የተጠቀሰውን ሥልጣን የተሰጣቸው ሕዝባዊ ድርጅቶች በመሆናቸው ነው ወይስ የመንግሥት መስተዳድር አካላት በመሆናቸው የሚሉ ጉዳዮች አከራካሪ ለመሆናቸው የሚያጠያይቅ አይደለም። በጸሐፊው አስተያየት ግን ሁለተኛው መስመር ማለትም ሥልጣኑ የተሰጣቸው የመንግሥት መስተዳድር አካላት በመሆናቸው ነው የሚለው መስመር የበለጠ ተደጋፊነት ያለው ይመስላል ።

የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ሴቶች ማህበርና የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ወጣቶች ማህበር ግን እላይ ለሕዝባዊ ድርጅቶች የተሰጡ ሥልጣናት የተሰጣቸው አይመስልም ።

ከዚህ በላይ የሕግ ማመንጨትንና፣የሕጎችና ደንቦችን አወጣጥ ተመልክተናል ። እስቲ ቀጥለን ደግሞ በማጠናቀሩ ፣ በማጽደቁ ፣ በመፈረሙና በማወጁ ሂደት የሚያጋጥሙ ሥነ ሥርዓቶችን እንመልከት ።

አብዛኛውን ጊዜ ሕጎች ጉዳዩ በሚመለከተው ሚኒስቴር ውስጥ ይረቀቃሉ። አንዳንድ ከሚኒስቴሮች ምክር ቤት ወይም ከርዕሰ—ብሔሩ ልዩ ትእዛዝ የሚመነጩ ሕጎች ግን የሚዘጋጁት በሚኒስቴሮች ምክር ቤት ሊቀመንበር ሥር በሚገኘው የሕግ ክፍል ውስጥ ነው ። በዚያም መጣ በዚህ ሕጉ ወደ ሚኒሲተሮች ምክር ቤት ይላካል ። የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ ከሚኒስቴሮች ምክር ቤት ምክትል ሊቀመንበር ጋር በመስማማት የሕጉ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ጉባኤ ወይም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥር በሚገኘው የሕግ ኮሚቴ በዝርዝር እንዲጠና ያቀርበዋል ። በተግባር እንደምናየው ወደ ሕግ ኮሚቴው ሳይቀርቡ በቀጥታ ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚቀርቡት ረቂቅ ሕጎች ከፍ ያለ የፖሊሲ ውሳኔ የሚጠይቁ ወይም በአስቸኳይ መታወጅ ያለባቸው ሆነው ሲገኙ ነው ። እንደነዚህ ዓይነቶቹን ረቂቅ አዋጆች ምክር ቤቱ በስፋት ከተወያየባቸው በኋላ ከፖሊሲ መመሪያዎች ጋር አጣምሮ ወደ ሕግ ኮሚቴው ይልካቸዋል ። በሌላ በኩል የፖሊሲ ውሳኔ የማያስፈልጋቸው መስለው የሚታዩ ረቂቅ ሕጎች ሲገኙ የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ ከምክር ቤቱ ምክትል ሊቀመንበር ጋር በመስማማት በቀጥታ ወደ ሕግ ኮሚቴው ይመራቸዋል ።

የሕግ ኮሚቴው ሊቀመንበር የሕግና ፍትሕ ሚኒስቴር ሲሆን ይህ ጽሑፍ ሲጠናቀር በአባልነት የተመደቡትም የሚከተሉት ነበሩ ።

ሀ/ የትምህርት ሚኒስቴር [9]

ለ/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

ሐ/ የገንዘብ ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር

መ/ የማዕድንና ኃይል ማመንጫ ምክትል ሚኒስትር

ሠ/ ከማዕከላዊ ፕላን ብሔራዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት አንድ ተወካይ

ረ/ ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊቀመንበር ቢሮ የሕግ ጉዳይ ኃላፊው

ሰ/ ረቂቁን ያቀረበው ሚኒስቴር ወይም ኮሚሽነር ።

ኮሚቴው ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት ለሥራው የሚያስፈልገውን ማናቸውንም የሚያገኘው ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊቀመንበር ቢሮ የሕግ ጉዳይ

መምሪያ ነው ። ሕጉ እንደገና እንዲረቀቅ የሚያስፈልግ ሆኖ ሲገኝም የሚሠራው ይህ መምሪያ ነው ። ኮሚቴው በዚህ አኳኋን በዝርዝር አጥንቶ የሚስማማበትን የ ሕግ ረቂቅ በኮሚቴው ሊቀመንበር በተፈረመ ደብዳቤ አባሪነት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ጉባኤ ያቀርባል ። በአባሪው ደብዳቤ ውስጥ በረቂቁ ላይ የተደረጉ ዓበይት ለውጦች ካሉ ፣ አከራካሪ የሆኑ ጉዳዮች አጋጥመው ከሆነ ፣ የተደረሰው ውሳኔና የኮሚቴው አስተያየት ይገለጻሉ ።

ሕግ በአወጣጡ ሂደት የሚጓዝበት ሥርዓት እላይ በተገለጸው መልክ ሲሆን ለየት ያለ መንገድ የሚከከተሉ ጥቂት ረቂቅ ሕጐች አሉ ። አንዳንድ ረቂቅ ሕጐች ይህንን ረቂቅ ያጠና ዘንድ ወደተቋቋመ ልዩ ኮሚቴ ይመራሉ ። አንዳንዴም ረቂቅ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከሕግና ከአስተዳደር ኮሚቴዎች ተውጣጥቶ ወደ ተቋ ቋመ ጥምር ኮሚቴ ወይም ከሕግና ከኢኮኖሚ ኮሚቴዎች ተውጣጥቶ ወደ ተቋ ቋመ ጥምር ኮሚቴ ሊመራ ይችላል ።

የሕግ ኮሚቴው ወይም ልዩ ኮሚቴው ወይም ጥምር ኮሚቴው ያጠናቀረውን ረቂቅ ሕግ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል ። የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ ከምክር ቤቱ ምክትል ሊቀመንበር ጋር በመስማማት ረቂቅ ሕጉ በምክር ቤቱ አጀንዳ ላይ እንዲሰፍር ያደርጋል ። ምክር ቤቱ በረቂቁ ሕግ ይወያያል ፤ ካጸደቀውም ለጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ እንዲቀርብ ያደርጋል ። ምክንያቱም ሕግ የማውጣት ሥልጣን ያለው የደርጉ ጉባኤ ነውና ። [10] ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ረ ቂቁን ሕግ ካጸደቀው ወደ ሚኒስትሮቹ ምክር ቤት ይልከውና ምክር ቤቱም በበ ኩሉ ሕጉ በነጋሪት ጋዜጣ ይታወጅ ዘንድ ወደ ምክር ቤቱ ሊቀመንበር ቢሮ ይል ከዋል ። ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚላከው የጸደቀው አዋጅ ቅጂ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ዋና ጸሐፊ ይፈረማል ። አዋጆቹ የሚወጡት በደርጉ ስም ይሆናል ። በረቂቁ ሕግ ላይ የሚኒስትሮቹ ምክር ቤት የሚያደርገው ለውጥ ቢ ኖር አስፈላጊውን ማስተካከል የሚፈጽመው በምክር ቤቱ ሊቀመንበር ሥር የሚ ገኘው የሕግ ጉዳይ መመሪያው ነው ።

ደንቦች ማለትም ሚኒስትሮች በአዋጅ በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት የሚ ያወጥዋቸው በደረጃ ዝቅ ያሉ ሕጐች እንዲጸድቁ ተብሎ ወደ ጊዜያዊ አስተዳደር ደርግ መላክ አያስፈልጋቸውም ። እነዚሁ ደንቦች የምክር ቤቱ ጉባኤ ካጸደቃቸው በነጋሪት ጋዜጣ ይታወጁ ዘንድ በቀጥታ ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊቀመን በር ቢሮ ይላካሉ ። ሲታወጁም ባወጣቸው ሚኒስቴር ወይም ኮሽነር ስም ነው የሚ ወጡት ።

የሕጐች በነጋሪት ጋዜጣ መታወጅ የሚመለከተው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊቀመንበር ቢሮ ሥር የሚገኘውን የሕግ ኮሚቴ መምሪያን ነው ።

<u>በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ወቅት</u>

<u>የአዋጅ አወጣጥ ሂደት በሠንጠረዥ ሲቀመጥ</u>

<u>(ልዩ ሁኔታ አልቀረበም ።)</u>

የሕግ አፍላቂው ሚኒስቴር ወይም ቢሮ (1)

የሚኒስትሮች ምክር ቤት (2)

(2.ሀ) በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕግ ኮሚቴ

(2.ለ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጉባኤ

(4) በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሊቀመንበሩ ቢሮ

(3) ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ

(5) ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት

<u>መፍቻ</u>

1. አፍላቂው ሚኒስቴር (ቢሮ) ረቂቁን አዋጅ አዘጋጅቶ ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ይልካል ።
2. ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ውስጥ የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ ከምክትል ሊቀ መንበሩ ጋር በመስማማት ረቂቁን አዋጅ ወደ ሕግ ኮሚቴው (2.ሀ) ወይም ወይም ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ጉባኤ ይልከዋል (2.ለ) ።
3. የሕግ ኮሚቴው የቀረበለትን ረቂቅ መርምሮና አስፈላጊ ከሆነ እንደገና አር ቅቆ ረቂቁን አዋጅ ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ጉባኤ ያቀርባል (2. ለ) ።
4. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጉባኤ (2.ለ) የተስማማበት ረቂቅ አዋጅ ይጸድቅ ዘንድ ወደ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ይላካል (3) ።
5. የጸደቀው ረቂቅ አዋጅ ወደ ምክር ቤቱ ተመልሶ ይላካል (2) ።
6. ምክር ቤቱም በበኩሉ አዋጁ በነጋሪት ጋዜጣ እንዲታወጅ ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊቀመንበር ቢሮ ይልከዋል (4) ።

## የግርጌ ማስታወሻዎች

* በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕግ መምሪያ ኃላፊ — ኤል. ኤል. ቢ. ሕግ ፋኩልቲ (አአዩ) ቀኃይ) ፣ ኤል. ኤል. ኤም. (ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ) ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሕግ ፋኩልቲ የትርፍ ጊዜ አስተማሪ ፤

1. ነጋሪት ጋዜጣ ፣ 34ኛ ዓመት ቁ. 1 ፣ አንቀጽ 5 እና 6 ።
2. ነጋሪት ጋዜጣ ፣ 34ኛ ዓመት ቁ. 1 ፣ አንቀጽ 4 ።
3. የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ አካል የሚከተሉትን ያጠቃልላል ።

   የደርግ አባላት በሙሉ የሚገኙበት ጠቅላላ ጉባኤ ፣ በጠቅላላው ጉባኤ የሚመረጡ አርባ አባላት የሚገኙበት ማዕከላዊ ኮሚቴና አሥራ ሰባት የደርግ አባላት የያዘ በጠቅላላው ጉባኤ የተመረጠ ቋሚ ኮሚቴ ። (የአዋጅቁ. 110/1969 ዓ.ም. አንቀጽ 2 ነጋሪት ጋዜጣ ፣ 36ኛ ዓመት ቁ. 13 ይመለከቷል። )
4. አንቀጹ እንደሚከተለው ይነበባል ፣ “ እያንዳንዱ ሚኒስትር የክፍሉን ሚኒስቴር ሥራ በሚገባ ለማካሔድና በርሱ ሥልጣን ሥር ያለውን ማናቸውንም ነገር በትክክል ለመፈጸም <u>የሚያስችለውን የሕግ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል ።</u>

   (ሠረዝ የተጨመረ) ፤
5. ነጋሪት ጋዜጣ ፣ 41ኛ ዓመት ቁ. 61 ።
6. ነጋሪት ጋዜጣ ፣ 41ኛ ዓመት ቁ. 3 ።
7. ነጋሪት ጋዜጣ ፣ 41ኛ ዓመት ቁ. 6 ።
8. ነጋሪት ጋዜጣ ፣ 40ኛ ዓመት ቁ. 15 ።
9. የትምህርት ሚኒስትሩ የኮሚቴው ምክትል ሊቀመንበር ነው ።
10. የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ኃላፊነት እንደገና ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 110/1969 ዓ ም አንቀጽ 5/6/ ፣ ነጋሪት ጋዜጣ ፣ 36ኛ ዓመት ቁ. 13 ፣ ይመለከቷል ።